ትምህርት 15

## የእግዚአብሔር ቃል ክፍል 2

### የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች

ሀ. ማር 4፡24 ምን እንደምትሰሙ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል፡፡ እንዲያውም ከዚያ የበለጠ ይጨመርላችኋል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ይህን ቃል በተናገረበት ወቅት የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል ይሰብክ ነበር፡፡ እርሱ የሚለውን የሚሰሙ የጊዜው የእግዚአብሔርን አሳብ እየሰሙ ነበር፡፡ ፈሪሳዊያኑ ደግሞ ክርስቶስ አሳች ነው እያሉ ይሰብኩ ነበር፡፡ ፈሪሳዊያንን የሰሙት ከእነርሱ ጋር አብረው ጌታን ይቃወሙ ነበር፡፡ ጌታን የሰሙት ግን ነፍሳቸውን ከማዳን ባሻገር አካላዊ ፈውስም ከልዩ ልዩ እስራትና ርግማንም ነጻ መውጣትን ይቀበሉ ነበር፡፡

የምንሰማው ቃል ትርጉሙ ያልተዛባ ትክክለኛና ሙሉውን የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ቃል መሆኑን ማረጋገጥ አለብን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተቱ መፅሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ስላባቸው ለትምህርታችን ተጽፈዋልና፡፡

አንዳንዶቹ ባለፉት አባቶቻችን የደረሰው በእኛ እንዳይደርስ ለማስጠንቀቅ የተጻፉ ናቸው፡፡ ብሉይ ኪዳንን ችላ ብንል በርካታ የተስፋ ቃሎቻችን ያሉት እዛ ውስጥ ነው፡፡ አዲስ ኪዳንን ትኩረት ባንሰጠው የተስፋ ቃሎች የሚወረሱት በኢየሱስ በኩል ብቻ ነው፡፡ የምናጠናው የሙሴን መጻህፍት፣ የነብያትን ትንቢት ወይም ብሉይ ኪዳንን ብቻ መሆን የለበትም፡፡ በአዲስ ኪዳንም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ መጻሕፍትና አርእስትም ተገቢውን ስፍራ ሰጥተን ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡

እስከመቼ ነው ጥቃቅን ጉዳይ በገጠመን ቁጥር ትንቢት የሚነገርበት ቦታ ፍለጋ እዚህና እዚያ የምንሄደው፡፡ መቼ ነው ራሳችንን ችለን በእምነት ጉዳያችን እግዚአብሔር ፊት አቅርበን የምናስፈጽመው፡፡

ይህን በዋናነት ማድረግ ያለባቸው የቃል አቅራቢዎቹ/አስተማሪዎቹ ቢሆኑም ምእመኑም የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት፡፡ እግዚአብሔር ከኔ የሚጠብቀው /በኔ ደስ ሚሰኘው/ ትንቢት የሚነገርበት ቦታ በማፈላለግ ብዞር ነው ወይስ ለእያንዳንዱ ሰው የህይወት መመሪያ እንዲሆን የሰጠው ቃሉ የሚለኝን ሰምቼ መተግበርን ብለማማድ ነው፣ በማለት ራሱን መጠየቅ አለበት፡፡ እኔ የነብያትን አገልግሎት እደግፋለሁ ነብያትን መቃወሜ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነ ይሄን ተናገር ያን አትናገር ብሎ መመሪያ የሚሰጠው የለም፣ የፈቀደውን በፈቀደው አገልጋይ ይናገራል፡፡ ግን እግዚአብሔር በነቢያት በኩል ምን ይናገረኛል ብሎ ሁሌ ከማሳደድ በተጻፈው ቃሉ ከገጠመው ጉዳይ ጋር የሚዛመደውን ክፍል ፈልጎ የሚለውን ተምሮ ተግባራዊ ማድረግን ቀዳሚ ስራ አድርጎ ከዚያ በኋላ ጉዳዩ መፍትሄ ካላገኘ ወደ ነቢያት ቢኬድ ክፋት የለውም፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚለን ሰው ቃሉ ከእግዚአብሔር መሆኑ የምንመዝነው በተጻፈው ቃሉ ነውና፡፡

እግዚአብሔር የርሱን ትክክለኛ ቃል ትምህርት የሚሰጥበት ስፍራ ፈልገው በመሄድ የሚሰሙትና የሚተገብሩት በሰፈሩት መስፈረያ መልሶ ሕይወትንና ፈውስን ይሰፍርላቸው እንደነበር ዛሬም ትክክለኛ ቃሉን ለሚፈልጉትና ለሚተገብሩት መልካም ነገርን ሁሉ ይሰፍርላቸዋል፡፡ እንዲህ ብናደርግ እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ ድንቆችና ታምራትን የሚያደርገው ቃሉን ለማጽናት ስለሆነ በየግላችን እንኳ ለምንጸልየው ጸሎት መልስ መስጠት ይጀምራል፡፡

ለ. ሉቃ 8፡18፣ እንግዲህ እንዴት እንደምትሰሙ ተጠንቀቁ ይላል፡፡ ስለዚህ እንዴት ነው መስማት ያለብን፡፡ ምሳ 4፡20-22፣ ነህ 8፡2-6፣ መክ 5፡1፣ ዕዝ 7፡10

1. **ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ (ልብን በማዘጋጀት)**፡- ዘጸ 19፡9-11፣ 22 የከበረ ሰው ፊት ስንቀርብ እዚህም እዚያም ቁሻሻ የነካው ልብስ ለብሰን እንደማንቀርብ እቤት ራስን መርምሮ በንስሃ መግባት በማስተካከል ወደ እግዚአብሔርን ማምለኪያ ስፍራ መሄድ፡፡
   ማቴ 5፡23-24 ለእግዚአብሔር መባ ከማቅረብ በፊት ባልንጀራህ ጋር የተፈጠረ አለመግባባት/መቀያየም ካለ አስቀድሞ እርሱን ማስተካከል፡፡ ተቀባይነት ያለው አምልኮ የሚጀምረው ጸሎት ቤት ከመምጣት

በፊት ነው፡፡ ሌላውን አሳዝነን፣ ቂም ይዘን ብንመጣ ንስሀ ባልገባነው ኃጢአት ምክንያት አእምሮዋችን ሊባክን ይችላል፡፡ በጸሎት ጌታ መንፈስ ቅዱስ የቃሉን ፍቺ እንዲገልጥልን እንድናስታውሰውም እንዲረዳን በመጸለይ። 1ዮሐ 2፡27፤ ዮሐ 16፡13

2. **በመፈለግ/በመጠማት፡-** 1ጴጥ 2፡2 አዲስ እንደተወለዱ ህጻናት የቃሉን ወተት ተመኙ/ፈልጉ/ተጠሙ (ዊሊንግሊ)፤ የመዳናችሁን ሙሉ በረከት በመውረስ እንድታድጉ፡፡ ዕብ 5፡13-14 በወተት ብቻ አትወሰኑ፤ ጠንካራ ምግብ/የጽድቅ ትምህርት መመገብ ራሳችሁን አስለምዱ፡፡
   የቃሉ ትክክለኛ ፍቺ መረዳትን; እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ባህርይ ተላቆ ከእርሱ ጋር ወደ ሰመረ ህብረት መድረስን በመፈለግ፡፡ ቃሉ እኛ በምድር ላይ ካሉ ከምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ የላቀ ዋጋ እንዳለው ክቡር እንደሆነ በመረዳት፡፡
   የምናመልከው አምላክ ይበልጥ እንድናውቀውና በሕይወታችን እንዲከብር በመፈለግ፡፡
   የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማወቅ በሃሰት ትምህርት ላለመጨረበርበር፡፡ እግዚአብሔር የሚናገረኝ ለራሴው ጥቅም ስለሆነ ለኔ እጅግ ጠቃሚ ነው በማለት ምክሩን በመጠማት፡፡ መድረክ ላይ ቆሞ የሚያስተምረው ሰው ቢሆንም እግዚአብሔር እንደተናገረን አድርገን በመቀበል፡፡ 1ተሰ 2፡13

እንደተሰላቸ፣ የእግዚአብሔርን ቃል አውቆ/ተግባር ላይ አውሎ እንደጨረሰ ሰው አለመሆን፡፡ ምድራዊ ተልዕኮውን ወይ ግዴታውን ሙሉ በሙሉ በመተግበር እንዳጠናቀቀ ሰው አለመሆን፡፡

3. **ነህ 8፡3 በጥሞና /ሙሉ/ያልተከፋፈለ/ትኩረት በመስጠት/ጆሮን ወደ ቃሉ በማዘንበል፡ የትምህርቱ ፍሬ ነገር እንዳያመልጥ በጥንቃቄ በ2ቱም ጆሮ መስማት (አቴንቲቭሊ)** ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንደ ወንዝ ውሀ ነው የሚያፈሰው፡፡ የወንዝ ውሀ ቆሞ አይጠብቅም፡፡ በጥሞና ካልሰማን እግዚአብሔር ለግላችን የሚናገረን ነገር ሊያመልጠን ይችላል፡፡ አጠገባችን ወዳለ ሰው ዞረን ምንድነው የተባለው፤ ስንት ገጽ ነው፤ ጥቅሱን ይዘሃል ...ብሎ ከመጠየቅ ሆን ብሎ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፡፡
4. **ነህ 8፡5-6፣ 9**፣ ዘፍ 18፡1-4፣ 27፣ ለመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ማንነት አክብሮታዊ ምላሽ በመስጠት፣ ቃሉም እጅግ ክቡር እንደሆነ በማወቅና በአክብሮት በማየት፡፡ 1ተሰ 2፡13 እግዚአብሔር እንደተናረ ቆጥሮ መቀበል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሰማየ ሰማያት ሊይዙት የማይችሉት አምላክ ቃል ነውና፡፡ 2ዜና 6፡18
5. ምሳ 4፡20-21-22፤ 7፡1-3፤ ወደ ልባችን በማስገባት ለማቆየት/ለማስታወስ/ለመያዝ በማሰብ (ሪቴንቲቭሊ)፡፡ በልባችን እስከሚሳል ድረስ እንዲሆን፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገው ቃሉ በልባችን ጽላት እንዲቀረጽ ነው፡፡ በልባችን እንዲቀረጽ ከፈለግን ደጋግመን ማጥናትና ማሰላሰል ይኖርብናል፡፡ ለማጥናት ደግሞ በጽሁፍ የሰፈረ ነገር ማስታወሻ በመያዝ፡፡
   ሮሜ 15፡4 በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረው የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ የተጻፈው ለትምህርታችን እንደሆነ ይናገራል፡፡ እንድንማረው የተሰጠን እስከሆነ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ስንማር እንደ ተማሪ ሆነን በመገኘት መጻፍ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደታዛቢ መሆን የለብንም፡፡ እኛ አንዴ የሰማነውን ለሁልጊዜ ስለ ማናስታውስ ባስፈለገን ጊዜ አገላብጠን ማየት የሚያስችለን ይሆናል፡፡ ምድራዊ/ሳይንሳዊ ትምህርት ቤትና ማሰልጠኛ ተቋማት ሲገባ ማስታወሻ አይያዝም ወይ፡፡ እዚያ ከምንማራቸው የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ ለዘላለም ሕይወት የሚያበቃ ስለሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይበልጣል፡፡

   በመጋቢዎች በቤተ ክርስቲያን ስለተሰጠው ትምህርት ፈተና መስጠት አልተጀመረም፡፡ እግዚአብሔር ግን እምነታችን ማደግ አለማደጉንና መታዘዛችንን ይመዝናል፡፡ ዓለምና ሰይጣን ጠልፎ ለመጣል ይፈትናል፡፡ ፈተና ለማለፍ ማስታወስና በተግባር መለማመድ ይጠይቃል፡፡

   ስንጽፍ ግን መጽሐፍ ቅዱስን መልሰን መገልበጥ ሳይሆን በእለቱ ከተማርነው የእግዚአብሔር ቃል ማብራሪያ ውስጥ በአዲስ መልክ የተረዳነውን ነው፡፡ ቀደምት አባቶቻችን ድንጋይ እየፋቁ ቅርጽ በማውጣት፣ በተጠረበ እንጨት፣ በበግና ፍየል ሌጦ ጥቅል በማዘጋጀት፤ የሚበጠበጥ ቀለም እየሰሩ በመቃ እያጠቀሱ ይጽፉ እንደ ነበር አንዘንጋ፡፡
   ይህን ያደረጉት እንዳይረሱት፣ በልባቸው እስኪቀረጽ ድረስ ደጋግመው እንዲከልሱት፣ እንዲያጠኑት ነው፡፡ መልሰው ለሌሎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲያካፍሉት ነበር፡፡ ለነርሱ እጅግ ውድና ክቡር ነበረ፡፡

6. ምሳ 4፡21፤ 25 ልባችን ብቻ ሳይሆን አይናችንም ሳይባክን ግራና ቀኝ ሳይሆን ወደ ተናጋሪው/ወደ ሚናገረን አምላክ/ቃሉን ወደ ሚያስተላልፍበት ሰራተኛ በማየት፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ቃሉ የሚለው ዓይነት ሕይወት/ባህርይ ያፈራ የሕይወት ግብ እና በዚሁ ምክንያት ልንወርሰው በላይ የተዘጋጀልን ርስት ታላቅ ውበት በዓይነ ሕሊና በማየት፡፡ ቆላ 3፡2
7. **የሰሙትን ከእግዚአብሔር የሆነ ቃል አምኖ ለመቀበል በመዘጋጀት** (ብሊቪንግሊ)፡፡ ዕብ 4፡2፣ ዮሐ 20፡ 30-31
2ነገ 7፡1-2 የሶርያ ንጉስ ቤንሀዳድ ሰራዊቱን ሁሉ ሰብስቦ ሰማሪያን በከበባት ጊዜ የእስራኤል ንጉስ የጦር አለቃ እግዚአብሔር በነብዩ ኤልሳ የተናገረው ቃል ስላላመነ እየተጋፋ በነበረው ሕዝብ ተረጋግጦ ሞተ፡፡ ይህ ሰው እግዚአብሔር የተናገረውን ላያምን ለምን የእግዚአብሔር ነብይ ጋ ደረሰ? ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር የተናፈረውን ቃል የሚሰማው /የሚያጠናው/ በማመን ለመቀበል ካልሆነ ከንቱ ነው፡፡
አለማመን፡-
   - የአመጻ ስራዎች ሁሉ መነሻና/መጸነሻ መወለጃም ነው፡፡
   - ኃጢአት እየበዛና እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል፤
   - መልካም ስራ ለመስራት አቅም ያሳጣል፤
   - የኢየሱስ ደም ከማያነጻቸው ኃጢአቶች አንዱ ነው፤
ይሂ ምእመኑን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን እጅግ ታዋቂ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ጭምር ይመለከታል፡፡ ዘሁ 14፡11፣ 20፡8-12 እግዚአብሔር ያለው ለአለቱ ተናገር ነው፡ ሙሴ ግን አለቱን 2 ቢዜ በበትሩ በመምታት ያልተባለውን አደረገ፡፡ ያልተባለውን ያደረገበት ምክንያት እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ስላላመነ ነው፡፡ ታምራት ሲያደርግ የነበረው በትሩን በመጠቀም ስለነበር ለአለቱ ብናገር ውሃ ስለማይወጣ ብሎ በበትርሩ መትቶ ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት የጀመረውን ታላቅ አገልግሎት ከግብ ሳያደርስ እርሱም የተሰጣቸውን ምድር በእግሩ ሳይረግጥ ቀረ፡፡
8. **ለመተግበር በመዘጋጀት** (ኦቢደንትሊ) ኢያሱ 1፡16-18፣ ያዕ 1፡22-25፣ ማቴ 7:20; 12፡50፤ ዮሐ 12:47፣ የእግዚአብሐርን ፈቃድ አውቆ አለመተግበር ፍርድ እንዳለበት በማወቅ፡፡
1ሳሙ 15፡22፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ ከመሰዋዕት ማድመጥም ከአውራ በግ ስብ ይበልጣል
እግዚአብሔር ከኛ የሚጠብቀው ቃሉን በመማር ተለውጠን ዓለምን እንድንለውጥ ነው፡፡ በፍሬያችን የኢየሱስ ተከታዮች መሆናችን እንዲታይ/እንዲታወቅ ነው፡፡ ማቴ 5፡14፣ ማቴ 7፡16-20፡፡ ተማሪ ከትምህርት ቤት የቀኑ የክፍል ትምህርት ተምሮ ሲወጣ የቤት ስራ ይዞ እንደሚወጣ እኛም ቢያንስ እሁድ የተማርነውን ልንከልሰውና ልንለማመደው ለትግበራ ትምህርት ቢያንስ ለአንድ ሳምንት መስክ እየወጣን እንደሆነ አንርሳ፡፡
ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ የተሰጠ 3ኛው መስጠንቀቂያ ተግባር ላይ አውሉት የሚል ነው፡፡
(I want you to affirm constantly, that those who have believed in God may be careful to devote themselves to good works). ቲቶ 3፡8፣ ዘዳ 5፡32 ዕብ 12፡25 2፡1፣ ማቴ 7፡12
ያዕ 1÷22 "ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታልሉ።"
ይህ ማለት በራሳችን ስራ ጸድቀን ለመዳን በሚል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በጸጋው አድኖናል ቀድሶናል፣ አጽድቆናል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስራ ላይ የምናውለው እምነታችን እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት/ለማረጋገጥ፣ ቅዱስ የሆነውን አምላካችንን ባሕርይ በመላበስ (ክርስቶስን በመምሰል) እንድናድግና የሰማያዊ ዜግነታችን ባህርይ ለዓለም ለመግለጥ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ቃሉን በመታዘዝ ስላከበርነው የሚከፍለን ወሮታ አለው፡፡ ይህን ለመተግበር የሚጠይቀው ፍላጎት፣ ምርጫ እና ውሳኔ ናቸው፡፡ መዝ 119፡30፣ 35
9. **ከልብ በሆነ ምስጋናና በጸሎት** (ሲንሰርሊ፤ ግሬትፉሊ፣ ፕሬየርፉሊ) የእ/ርን ቃል ለመስማት/ለመማር ስንጀምርና ስንጨርስ በምስጋና በጸሎት መሆን አለበት

ለቃሉ የተገባ ክብርና ስፍራ ሰጥተን በመስማት/በመማር በማመንና በመተግበር ስንለማመደው ከእግዚአብሔር ጋር ራሳችን ያለ ሌላ ሰው ድጋፍ/ጸሎት በቀጥታ መገናኘት ወደ መቻል ያደርሰናል፡፡

ፈጠን ብለን ብዙ ገጾች በአንድ ቀን ከማንበብ ይልቅ እየገባን እያሰላሰልነው ብንሄድ ይሻላል፡፡

**የእግዚአብሔር ቃል ለኛ ያለው ጠቀሜታ**

መጽሐፍ ቅዱስ የጠቅላላው የሰው ዘር ሁሉ የተናጠልና የወል ችግር ትክክለኛ መንስኤና መፍትሔ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ብቸኛ መጽሐፍ ነው፡፡

እግዚአብሔር የችግራችን ምክንያት እኛው ራሳችን መሆናችንን ማሳየት ብቻ ሳይሆን ከታላቅ ጸጋው የተነሳ ለችግራችን ሁሉ መፍትሔ (መድኃኒት) አዘጋጅቶ ጨርሶ በነጻ ወስዳችሁ ተጠቀሙበት ብሎ ቃሉን ሰጥቶናል፡፡ የኛ ድርሻ ይህን የቃሉ መድኃኒት በፕሪስክሪፕሽኑ መሰረት መስማትና በእምነት ከራሳችን ጋር በማዋሃድ ማስወገድ የሚገባንን ሁሉ በማሰወገድ መገላገል፣ በጠላት ከመጠቃት ወደ ማጥቃትና መውረስ መሸጋገር ያስችላል፡ ፡

የእግዚአብሔር ቃል በእምነትና ስራ ላይ በማዋል ወደ ሚያስፈልገን ነገር ሁሉ የምንመነዝረው የበረከታችን ሁሉና የእግዚአብሔር ኃይል መጋዘን ነው ማለት ይቻላል፡፡

**በውስጡ ከተከማቸው ኃይል የተነሳ ለኛ ከሚያከናውናቸው ብዙ ነገሮች ጥቂቶቹ እነሆ፡ -**

1. እግዚአብሔርን እንድንመካበት፣ እንድንወደውና፣ እንድናከብረው /እንድንፈራው/ የሚያደርጉት ወሰን አልባ ታላቅ ማንነቱን (ባሕሪያቱን) ዘርዝሮ ያስታውቀናል፡፡ በእግዚአብሔር ማንነት ላይ በእውነት የተመሰረተ እምነት እንዲኖረን ያስችላል፡፡ እግዚአብሔር ራሱን በተብራራ ሁኔታ ለሰው ዘር የሚያስተዋውቅበት ዋነኛ መንገድ በጽሁፍ የሰፈረው ቃሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ አምላክ መሆኑን፣ ሌላው ሁሉ እርሱ የፈጠረውና የሚገዛው ፍጥረት መሆኑ ካወቅን ከንቱ የሆኑ የተለያዩ ጣኦታትን ለማምለክ ልባችን እንዳያዘነብል ያግዛል፡፡
   ከእግዚአብሔር የሆነው ያልተበረዘ ዕውነት የምናውቅበት ዋነኛ መንገድ ነው፡፡
   ሰዎች ከከበባቸው መንፈሳዊ ጨለማና እንቅልፍ እንዲባንኑ ያደርጋል ሐሥ 2፡27፣ ሮሜ 1፡16
   መዳን የሚገኝበት ጥበብ በማሳወቅ ወደ መዳን መንገድ ይመራል፡፡ 2ጢሞ 3፡15
   የእግዚአብሔር ቃል የአግዚአብሔር ዕውቀትና ጥበብ ስለሆነ ማስተዋልን/መንፈሳዊ መረዳትንና፣ ጥበብን በማሰገኘት የምናመልከው አምላክ እግዚአብሔርን ይበልጥ በማወቅ እያደጉ ለመሄድ ያስችላል፤ መዝ 119፡105፣ 130 (ከሳይንሳዊ ትምህርት ይለያል-ሳይሳዊ እውቀት መንፈሳዊ መረዳትን አያስገኝም፡፡ ብዙ ሳይንሳዊ እውቀት ያላቸው ሰዎች በመንፈሳዊ ነገር ሞኞች ናቸው)፡፡
2. በዘመናችን ሁሉ ምን ጊዜም መልካም እንዲሆንልን በእግዚአብሔርና በሰው ፊት እንዴት መኖር እንዳለብን በተብራራ ሁኔታ ያስተምራናል/ ያሰለጥለናል/ይመራናል፡፡ ዘዳ 6፡24፣ መዝ 119፡105፣ 1ጢሞ 4፡11-13
   በእግዚአብሔር አባታዊ ምክርና መመሪያ መሰረት መኖር ደግሞ በዚህ ምድርም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ታላቅ ክብርን ያስገኝልናል፡፡ ምሳ 4፡20-22
   ለሕይወታችን ሥኬታማነትን ያስከትላል/የስኬታችን ቁልፍ ነው፡፡ ኢያ 1፡8፣ መዝ 1፡1-3
   የባህርይ ለውጥ ለማምጣትና ለመልካም ስራ ሁሉ ዝግጁዎች መሆን ያስችላል፡፡ 2ጢሞ 3፡16-17፣ ሮሜ 12፡1-3፣
3. በእግዚአብሔር እይታ እኛ የሰው ልጆች ማን እንደ ሆንን፣ በእግዚአብሄር ችሎታ ተደጋፊነታችን ምን ያህል ሰፊ መሆኑን ያሳየናል፡፡ አምላካችን ከእኛ የሚጠብቀው (የሚፈልገው) ምን እንደሆነ ያሳውቀናል፤ እግዚአብሔር የክብር ስፍራ ሰጥቶ የፈጠረን ሆነን ሳለ በኃጢአት ምክንያት ለሰው ዘር ሁሉ ካዘጋጀው መልካም ነገር በመጉደል የዘላለም ሞት ፍርድ በራሳችን ድርጊት ስላመጣን በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን የተከፈለልን ዋጋ ምንኛ ታላቅ መሆኑን የምናይበት መንፈሳዊ መስታወታችን ነው፡፡ ያዕ 1፡23-25 ቃሉን ስንማር የራሳችን ሕይወት ቆሻሻ ያሳየናል፡፡ ፊታችንን በመስታወት የምናየው ቁሻሻ ካለ አይተን ልናስወግድ እንደመሆኑ መጠን የእግዚአብሔር ቃል ስንማር የሚያሳየን ውስጣችን የተደበቀ ቁሻሻ በማስወገድ በሚነግረን የጽድቅ ስራ ከተካን በቅድስና እያደግን እንሄዳለን፡፡ 1ዮሐ5፡13

4. የጠላቶቻችን ማንነትና ማሸነፍያው መንገድ ምን እንደሆነ ያሳውቀናል፡፡ ቃሉ መንፈሳዊ የጦር መሳሪያችን (ሰይፍ) ሆኖ ያገለግለናል ኤፌ 6፡11-18፣ 2ቆሮ 10፡4-5፡፡ አርነትም ያወጣል፡፡ ዮሐ 8፡31-32

5. የእምነት መገኛ ነው፡፡ እምነት ከሌለ እምነት ለማግኘት በፕሪስክሪፕሽኑ መሰረት ቃሉን መስማትና ድምጽ አውጥቶ ማንበብ ነው፡፡ ሮሜ 10፡17፣
   እምነታችን በእውነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በእውነት ላይ ያልተመሰረተ እምነት አያድንም፡፡ ደካማ እምነት ቃሉን ተግባር ላይ ያለማዋል ውጤት ነው፡፡ እምነት እያደገ እንዲሄድ ቃሉን መስማትና መተግበር ነው፡፡
   አሸናፊነት/የጸሎት መልስ የሚያስገኝ እምነትም ፍጹም ዕውነት በሆነው የእግዚአብሔር ቃል ላይ መመስረት አለበት፡፡ እውነተኛ እምነት ጋራንቲ ያስፈልገዋል፡፡ ስለሚፈልጉት ጉዳይ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠ ተስፋ ቃል መኖሩን ፈልጎ ማግኘትና የተስፋ ቃሉን ከፍቶ በእግዚአብሔር ፊት በንባብ ማሰማት፡፡ (ለምሳሌ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማቴ 7፡11፣ ሐሥ 2፡39፡፡) አነሆ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ አኔ በክርስቶስ ኢየሱስ የዳንኩኝ ልጅህ ነኝ፡፡ በዚህ በሰጠኸው የተስፋ ቃልህ መሰረት ይህን የኔ ጉዳይ እንድትፈጽምልኝ እለምንሀለሁ ማለት፡፡ ቀጥለን በ1ዮሐ 5፡14-15 መሰረት ከተንበረከክንበት ተነስተን የለመንኩት ነገር እጄ ይገባል በማለት እግዚአብሔርን ማመስገን ነው፡፡
   በሕይወት ጉዟችን የሚገጥሙን ውጣ ውረዶች ተቋቁመን ማለፍ እንድንችል ያነቃቃናል; ያበረታታናል፡፡ 1ቆሮ 10፡13፣ መዝ 119፡50፡፡

6. እግዚአብሔር ምን እንዳደረገልን፣ አሁን እያደረገልን ያለው እና ወደፊት ምን ሊያደርግልን እንደሚችል ወይም እንዳቀደ ውሉታውንም ዘርዝሮ በመንገር ከእርሱ ጋር ኅብረታችን እንዲያምር ያስችላል፡፡
7. የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ በሰው ሰራሽና ሀሰተኛ ትምህርት በመታለል ሕይወታችንን ከማበላሸት ያስጥለናል፡፡ ማቴ 22፡28፣ ኤፌ 4፡14፣ መዝ 37፡30-31፣ 119፡11
   ኢዮ 34፡3-4፣ ምላስ ምግብን አጣጥሞ እንደሚለይ፣ ጆሮም (በአእምሮ አማካይነት) የንግግርን ለዛ ለይቶ ያውቃል። [4] የሚበጀንን እንምረጥ፣ መልካሙንም አብረን እንወቅ።
8. መንፈሳዊ ህይወታችንን ይመግባል/በመልካም ባህርይ ይገነባል ማቴ 4፡4፤ ዕብ 5፡12-14፣ ሐሥ 20፡32
   ለሁሉም የሕወታችን ደረጃዎች ምግብ አለው፡፡ አዲስ የተወለደ ህጻን እየጠነከረ እንዲሄድ ቃሉን ወተት መመገብ ነው፡፡ ቃሉ መወለጃ ነው፣ ለህጻኑ ምግብም ቃሉ ነው፡፡ አለዚያ እየገረጣ ሄዶ ይሞታል፡፡ ለህጻንነታችን - ወተት 1ጴጥ 2፡2፣ ከዚያ ከፍ ስንል - ዳቦ ማቴ 4:4፣ ከዚያ ከፍ እያልን ስንሄድ - ጠንካራ ምግብ ዕብ 5፡13-14 ጠንካራ ስጋን ማኘክና አጥንት መቆርጠም ወደ መቻል መድረስ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል መተግበር መለማመድ ነው ወደ ሙሉ መንፈሳዊ ሰው፣  ወደ አደገ እምነት የሚያደርሰን፡፡
   እግዚአብሔር አዲስ ልደት ከሰጠን በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት በመተግበር ሳናቋርጥ እየጨመርን ካልሄድን እምነታችን በዚያው ባለበት ይቆምና እያደር እየደከመ ይሄዳል፡፡ በያመቱ ያው ህጻን መሆን ያስከትላል፡፡ ቀድሞ የነበረ ደስታና የማመስገን ሕይወት ወደ ማጉረምረምና ጥርጣሬ እየተለወጠ ይሄዳል፡፡ በዚያው ከቀጠልን ከእምነት ወደኋላ ማፈግፈግ/በጠላት መልሶ ወደ መማረክ ሊያስከትል ይችላል፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)                    2018 ዓ. ም.